DC | DEPARTMENT of HUMAN SERVICES

# የተሻሻሉ እና በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች (FAQ) ስለ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት (DC) የወረርሽኝ ኤሌክትሮኒክስ ጥቅማጥቅሞች ማስተላለፊያ (P-EBT) ፕሮግራም

*ይህ FAQ (በየጥ) የ DC P-EBT ፕሮግራም ላይ በጣም ወቅታዊ የሆነ መረጃ ይዟል። እርሱ እንደአስፈላጊነቱ ይሻሻላል። ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉት፣ እባክዎ dhs.dc.gov/p-ebt ይጎብኙ ወይም ለጥሪ ማእከሉን በ 877-4DC-PEBT (877-432-7328) ወይም TTY፥ 711፣ ሰኞ – ዓርብ፣ 7:30 ጧት – 4:45 ከሰዓት (EST) ይደውሉ።*



**ማሻሻያ፥**: በፌብሯሪ 2, 2021፣ የፌዴራል መንግስት የ2020 የተሻሻለው የቤትሰቦች የመጀመሪያ ኮሮናቫይረስ ምላሽ ሕግ (የP-EBT ፕሮግራምን በማርች 2020 ውስጥ የፈቀደው) ላይ መመሪያ አውጥቷል፣ USDA ብቁ በሚያደርጉ ሁኔታዎች ስር P-EBT ጥቅማጥቅሞች መስጠትን ለመቀጠል የስቴት እቅዶችን እንዲያጸድቅ የሚፈቅድ። የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ (OSSE) የዲስትሪክት ቢሮ እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ (DHS) የስቴት እቅዱን አስገብተው በማርች 23, 2021 ፈቃድ አገኝቷል። ይህ ፈቃድ ዲስትሪክቱ P-EBT program from ከኦክቶበር 2020 እስከ ጁን 2021 የP-EBT ፕሮግራምን እንዲቀጥል ያደርጋል፣ እድሜያቸው ለትምህርት ቤት በጣም ያልደረሰ ህጻናትን ጨምሮ፣ ከሜይ 2021 በመጀመር። (የሴፕቴምበር 2020 ጥቅማጥቅሞች በፀደይ ወይም በጋ 2021 ውስጥ ተሰጥቷል።) ቀጥሎ ያሉት ጥያቄዎች እና መልሶች ያሁኑን ፕሮግራም ይገልጻሉ።

## 1. የP-EBT ጥቅማጥቅሞች ምንድን ናቸው?

- P-EBT በአገር አቀፍ የትምህርት ቤት የምሳ ፕሮግራም (NSLP) መሰረት ነጻ ወይም ዋጋቸው ቅናሽ የሆኑ ምግቦች በትምህርት ቤታቸው ያገኙ እና በCOVID-19 የፌዴራል አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት ብቁ የሚያደርግ የቪርቷል ወይም ጥምር ትምህርት ቤት እየተከታተሉ ያሉ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ጊዜያዊ የፌደራል የምግብ ጥቅማጥቅም ነው።

## 2. የP-EBT ጥቅማጥቅሞችን ማን ያገኛል?

- ለነጻ እና ቅናሽ-ዋጋ ምግቦች ለትምህርት ዓመት (SY) 2020-2021 በልጁ ትምህርትቤት የተሰራ የቤተሰብ ማመልከቻ በማስገባት አማካኝነት ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ህጻናት።
- የማህበረሰብ ብቃት መስጫ(CEP) ትምህርት ቤት ወይም በድንጋጌዎች 2 ወይም 3 ሥር የሚሰራ ትምህርት ቤት ውስጥ የተመዘገቡ ህጻናት።
- ተጨማሪ የምግብ እርዳታ ፕሮግራም (SNAP) ቤተሰቦች ውስጥ ለ2020-2021 ትምህርት ዓመት ብቁ የሆኑ ህጻናት።
- ገንዘቦቹ የሚተላለፉ አይደሉም።




## 3. ልጆች ብቁ ከሆኑ፣ ምን ያህል ገንዘብ ያገኛሉ?

- P-EBT በትምህርት ቤታቸው ማግኘት ይችሉ ለነበሩ ብቁ ለሆኑ ልጆች፣ በሳምንት ለአምስት ቀናት፣ ቁርስ፣ ምሳ፣ እና ማቆያ ለመሸፈን የታሰበ ነው። ለ2020-2021 ትምህርት ዓመት ጥቅማጥቅሞቹ $122.76 በወር ለምዝገባው ሙሉ ቪርቿል ወር ወይም $73.66 በወር ለምዝገባው ሙሉ የድቅል ወር ይገመታል።
  - ከኦክቶበር 1, 2020 እስከ ጃኗሪ 31, 2021 ላሉ ጥቅማጥቅሞች፣ ሁሉም ብቁ የሆን ተማሪዎች $122.76 በወር ይቀበላሉ።
  - ከፌብሯሪ 1, 2021 በኋላ ላለው፣ የተማሪ ጥቅማጥቅሞች የልጁ የትምህርት ሁኔታ ላይ ይመሰረታል። ተማሪዎች $122.76 ለእያንዳንዱ ብቁነት ወር ሙሉ በሙሉ ቪርቷል ቪርቿል በሆነ ትምህርት ቤት ወይም $73.66 በወር በድቅል ትምህርት ቤት ያገኛሉ።
- ከፌብሯሪ 1, 2021 በኋላ፣ የአሰራር ሁኔታ የትምህርት ቤት ደረጃ ውሳኔዎች ላይ እና የመላው-ዲስትሪክት ሁኔታ ያልሆነው ላይ ሲመሰረት፣ ትምህርትቤቶች እንደ "ሙሉ በሙሉ ቪርቿል" የሚወሰዱት ለሁሉም የተመዘገቡ ተማሪዎች ካሉት የትምህርት ቀናት ከ50% በታች በቪርቿል ሲደረጉ ነው። ለሁሉም የተመዘገቡ ተማሪዎች ካሉት የትምህርት ቀናት ከ50% ወይም ከዚያ በላይ በ-አካል ሲደረጉ፣ ትምህርትቤቱ “የድቅል/ጥምር” ሁኔታ ውስጥ እንዳለ ይወሰዳል እና ያንን ትምህርት ቤት የሚከታተሉ ሁሉም ተማሪዎች የድቅል

ጥቅማጥቅም ተመን ያገኛሉ።

4. **ባሁን ጊዜ ለነጻ ወይም ቅናሽ-ዋጋ ምግቦች ያልበቁ የዲስትሪክት ቤተሰቦች እንዴት ያመለክታሉ?**
   - የDCPS CEP ትምህርትቤት የሚከታተሉ ልጆች ቤተሰቦች ለነጻ ወይም ቅናሽ-ዋጋ ምግቦች ወዲያውኑ ብቁ ይሆናሉ። የDCPS CEP ትምህርት ቤቶች ዝርዝር በ dcps.dc.gov/page/community-eligibility-provision-cep-schools ሊገኝ ይችላል።
   - የፌዴራል የነጻ እና ቅናሽ-ዋጋ ምግቦች ፕሮግራም (FARM) የሚያስተናግድ የDCPS CEP ትምህርት ቤት የሚከታተሉ ልጆች ያላቸው ቤተሰቦች ተጨማሪ መረጃን በ dcps.dc.gov/publication/free-and-reduced-priced-meals-farm-application ማግኘት ይችላሉ።
   - ትምህርት ቤታቸው የፌዴራል FARM ፕሮግራም ውስጥ እንደሚሳተፍ እርግጠኛ ያልሆኑ ቤተሰቦች ለFARM ማመልከት ይችሉ እንደሆነ ለማወቅ የልጃቸው ትምህርት ቤትን ማግኘት አለባቸው። ይህ የህዝብ እና የቻርተር ትምህርት ቤቶችን ይጨምራል።

5. **ቀድሞውኑ SNAP ወይም TANF የሚቀበሉ ቤተሰቦች P-EBT ጥቅማጥቅሞችን እንዴት ያገኛሉ?**
   - SNAP ወይም ጊዜያዊ እርዳታ ለፈላጊ ቤተሰቦች (TANF) የሚቀበሉ ቤተሰቦች ውስጥ ላሉ ብቁ ለሆኑ ህጻናት፣ P-EBT ጥቅማጥቅሞች ወዲያውኑ የቤተሰቡ ነባር EBT ካርድ ላይ ይጫናሉ። ምንም ዓይነት እርምጃ ከSNAP ወይም TANF ደንበኞች አይፈለግም።




6. **SNAP ወይም TANF የማይቀበሉ ቤተሰቦች P-EBT ጥቅማጥቅሞችን እንዴት ያገኛሉ?**
   - SNAP ወይም TANF የማይቀበሉ ቤተሰቦች ውስጥ ላሉ ህጻናት፣ ለብቻ የሆኑ በP EBT ጥቅማጥቅሞች አስቀድሞ-የተጫኑ የEBT ካርዶች በጸደይ እና በጋ 2020 ወቅት ወደ ቤቶቻቸው ተልከዋል እና የሴፕቴምበር 29ኛ ክፍያ በእነዚያ ካርዶች ላይ ተጭኗል።. ምንም አዲስ ካርዶች ለሴፕቴምበር ክፍያ አልተላኩም።
   - አንድ ቤተሰብ መጀመሪያ የተሰጠውን ካርድ ማቆየት ካልቻለ፣ ለFIS የዲስትሪክቱ EBT አጋር በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት በነጻ የስልክ መስመራቸው (888) 304-9167 በመደወል አዲሱን መጠየቅ ይችላሉ።

7. **የኦክቶበር 2020 ጥቅማጥቅሞች ለምንድን ነው በፀደይ 2021 ውስጥ እየተሰጡ ያሉት?**
   - በኦክቶበር 1, 2020 ላይ፣ የፌዴራል መንግስት የ2020 የቤትሰቦች የመጀመሪያ ኮሮናቫይረስ ምላሽ ሕግ፣ የP-EBT ፕሮግራምን የፈቀደው፣ ላይ ማሻሻያ አድርጓል፣ USDA ብቁ በሚያደርጉ ሁኔታዎች ስር P-EBT ጥቅማጥቅሞች መስጠትን ለመቀጠል የስቴት እቅዶችን እንዲገመግም የሚፈቅድ።
   - ዲስትሪክቱ የUSDA መመሪያን በኖቬምበር 16, 2020 ተቀብሏል። ቀጣይነት ያለው የምደባዎች ሕግ፣ 2021 P EBTን እስከ ሴፕተምበር 2021 መጨረሻ ያራዝማል። ያ ማለት P-EBT አሁን ለሁሉም 2020-2021 ትምህርት ዓመት (SY) ይገኛል።
   - የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ (OSSE) የዲስትሪክት ቢሮ እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ (DHS) የስቴት እቅዱን አስገብተው P-EBTን ለዲስትሪክቱ ቤተሰቦች ማስፈጸም ለመጀመር በ3/23/2021 ከU.S. የግብርና መምሪያ (USDA) ፈቃድ አገኝቷል።
   - ዲስትሪክቱ ከኦክቶበር እስከ ዲሴምበር 2020 በፀደይ ውስጥ ክፍያን ይሰጣል።



**8. ቤተሰቦች የP-EBT ጥቅማጥቅሞች እንደሚደርሳቸው እንዲያውቁ ይደረጋሉ?**

- አዎ። መስጫ የሚደረግበት ጊዜ ማስታወቂያዎች የP-EBT ጥቅማጥቅሞች ለደረሳቸው ሁሉም ቤተሰቦች ይላካሉ።
- አዎ። መስጫ የሚደረግበት ጊዜ ብቁ የሆኑ ቤተሰቦችን ለማሳወቅ የሮቦ-ጥሪዎች ይደረጋሉ።
- ቤተሰቦች በተጨማሪም ቀሪ ሀሳባቸውን ለማወቅ፣ ሁልጊዜ በ www.ebtedge.com ውስጥ መግባት ወይም ነጻ የEBT ኤጅ መተግበሪያን ከአፕል ክምችት ወይም ጉግል መጫወቻ ክምችት ማውረድ ይችላሉ።

**9. ቤተሰቦች በP-EBT ጥቅማጥቅሞች ምን መግዛት ይችላሉ?**

- የP-EBT ጥቅማጥቅሞች ልክ እንደ የSNAP የምግብ ጥቅማጥቅሞች ይሰራሉ። የP-EBT ጥቅማጥቅሞችን የሚቀበሉ ቤተሰቦች ገንዘቡን ምግብ ብቻ ለመግዛት መጠቀም ይችላሉ። የእነዚህ ጥቅማጥቅሞች ዓላማ በትምህርት ቤታቸው ማግኘት ይችሉ ለነበሩ ልጆች ምግቦችን ለመስራት ለምግብ መግዣ ገንዘብ መስጠት ነው።

**10. የP-EBT ጥቅማጥቅሞች የት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ?**

- የP-EBT ጥቅማጥቅሞች ከማንኛውም የSNAP መደብር ምግብ ለመግዛት መጠቀም ይቻላል። አብዛኛዎቹ የችርቻሮ ነጋዴዎች SNAP ወይም EBT የሚቀበሉ መሆኑን የሚገልጽ ምልክቶች አላቸው። ፍቃድ ያላቸውን የ SNAP የችርቻሮ ነጋዴዎችበ fns.usda.gov/snap/retailer-locator ተዘርዝሯል።
- በተጨማሪ የ EBT ካርዶችን የሚቀበሉ የችርቻሮ ነጋዴዎችን ለማግኘት www.ebtedge.com መጎብኘት ወይም የ EBT Edge የሞባይል መተግበሪያን ከአፕል ወይም የጉግል ጨዋት ክምችት ላይ ማውረድ ይችላሉ።
- የP-EBT ጥቅማጥቅሞች በተጨማሪ የኦንላይን የምግብ ግዢዎችን ለማስረከቢያ ከ Amazon እና Aldi ለመፈጸም ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ በ፥ https://www.amazon.com/snap-ebt/ ወይም shop.aldi.us/ ይገኛል።



**11. የP-EBT ጥቅማጥቅሞች በደረሱበት ወር ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው?**

- አይደለም። ገንዘቡ ከአንድ ወር ወደሌላው ወር ይተላለፋል። ለአንድ ዓመት በላይ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ጥቅማጥቅሞች ከካርዱ ይሰረዛሉ።

**12. ቀድሞውኑ-የተሰጠ የEBT ካርድ ጠፍቶ ወይም ተቀርጦ ከሆነስ?**


- ለጉዳይ-የተለዩ ጥያቄዎች እባክዎ በ 877-4DC-PEBT (877-432-7328) or TTY፥ 711፣ ሰኞ – ዓርብ፣ 7:30 ጧት – 4:45 ከሰዓት (EST) ይደውሉልን።

**13. P-EBT ማግኘት የቤተሰብን "የህዝብ ድጋፍ" ሁኔታ ላይ ጉዳት ያስከትላል?**

- አይደለም። የ P-EBT ጥቅማጥቅሞችን መጠቀም የወላጆችን ወይም የልጆቻቸውን የስደተኝነት ሁኔታ ላይ ጉዳት አያስከትልም። የህዝብ ድጋፍ ህጉ ለ P-EBT ጥቅማጥቅሞች ተፈጻሚ አይደለም።

**14. ተጨማሪ መረጃ የት ይገኛል?**

- የDHS የP-EBT ገጽን፥ dhs.dc.gov/p-ebt ይጎብኙ።
- ለጉዳይ-የተለዩ ጥያቄዎች እባክዎ በ 877-4DC-PEBT (877-432-7328) or TTY፥ 711፣ ሰኞ – ዓርብ፣ 7:30 ጧት – 4:45 ከሰዓት (EST) ይደውሉልን።



**እነዚህ ቁሳቁሶች በአስቸኳይ ምግብ ለሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች ይገኛሉ፥**

| **ሀብት** | ስልክ ቁጥር | ድረገጽ |
|---|---|---|
| የDC (ዲሲ) የኮሮናቫይረስ የምግብ መረጃዎች ገጽ | | https://coronavirus.dc.gov/food |
| Capital Area Food Bank | (202) 644-9800 | https://www.capitalareafoodbank.org/ |
| So Others Might Eat (SOME) | (202) 797-8806 | https://www.some.org/ |
| Bread for the City | (202) 265-2400 | https://breadforthecity.org/ |

64 New York Avenue, NE
Washington DC 20002